## "ትውልድ" በሚል ርእስ ይታተማል ለተባለ "የወጣቶች የስፖርትና ባህል ሚንስቴር" መጽሔት በግብዣ የተሰጠ የፅሁፍ ኢንተርቪው

## 1. "ትውልድ" በእርስዎ አመለካከት ምን ፍች ይሰጠዋል?

የአለቃ ኪዳነ ወልድ መዝገበ ቃላት፥ ትውልድ የሚለውን ቃል፥ በመጀመሪያ "በቁሙ፤ ዘር ልጅ፤ ባላገር ተወላጅ" ብሎ ይፈታዋል። ቀጥሎ ደግሞ፥ "ወገን ነገድ፤ ሐረግ" ይለዋል። በመጨረሻም፥ "የሰው አወላለድ የዘር አወራረድ ሸቅብና ቁልቁል የሚቆጠር፤ በተራ የሚጣፍ የሚነገር፤ የሰው ዕድሜ ዘመን መዋዕል፤ ተወልዶ እስኪሞትና እስኪቀበር ተሹሞ እስኪሻር የሚኖረው።" (ገፅ 39?) ይላል። የደስታ ተክለ ወልድ መዝገበ ቃላት ደግሞ "የሰው ወገን ነገድ ጎሣ" ይለውና ቀጥሎ "የተወለዱበት የዘር አገር" (ገፅ 436) ይለዋል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ፍችዎች አሁን በምንነጋገርበት አውድ የምናስበውን ፍች ቁርጥ ባለ መንገድ የሚያመለክቱ አይመስለኝም።

መዝገበ ቃላቱን አኑረን፥ ጆሯችንን ደጋግመን ወደ እለት ተእለት ውይይት ጣል ስናደርግ ግን ለየት ያለ ቁምነገር እናገኛለን። ለምሳሌ፥ በእኛ ሀገር፥ ሰዎች ሲናገሩና ሲፅፉ፥ "የእኛ ትውልድ"፥ "ያ ትውልድ"፥ "ይሄ ትውልድ"፥ "በእኛ ጊዜ"፥ "በእኛ ዘመን" እያሉ፥ ብዙ ጊዜ ስለነበሩበትና ስላሉበት የኑሮ ሁኔታ በጥቅሉ ያወጋሉ። ስላለፈው ዘመን ሲያወሱ፥ ብዙ ጊዜ ኑሮ ርካሽ እንደነበር ይተርካሉ። ዘመናቸው፥ ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበረበት፥ ሕግ የተፈራና የተከበረበት፥ ስነምግባርና ስነስርዓት ጥብቅ የነበረበት፥ የተሻለ መፈቃቀርና መተሳሰብ የሰፈነበት ወዘተ. እንደነበረ፤ ሰዉም የዋህ፥ ቅን፥ ደግ፥ መንፈሰ ጠንካራ እንደነበረ፤ በአካላዊ ብቃትና ጥንካሬም የሚደነቅ እንደነበረ ይናገራሉ። ብዙ ጊዜ፥ ዘመናቸውን ባንድ ልቦለድ ውስጥ እንደሚሳል ገፀባህርይ ይስሉታል ማለት ነው። እውነትም፥ የተጋነነ ነገርም ይናገራሉ። አሳሳላቸውን የሚወስኑ ብዙ ግላዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች አሉ። ይሁን እንጂ ስለዘመናቸው ጎልተውና በተደጋጋሚ የሚነገሩ የጋራ ነቁጦች ሊኖሩ ይችላሉ። ወይም ደግሞ ዘመኑ የሚታወቅበት ገናን ባህርይ ወይም ባህርያት ሊኖሩት ይችላሉ።

ይህንን ጥያቄ መጀመሪያ ሳነብ፥ ወዲያው ያሰብኩት፥ **"ትውልድ" የሚለው ቃል፥ በተወሰነ ጊዜና ቦታ የኖሩ ወይም በመኖር ላይ ያሉ፥ ከሞላ ጎደል የጋራ የሆነ አመለካከት፥ ተግባር፥ ምኞት፥ ስነምግባር ወዘተ. ያላቸውን ወገኖች የሚገልፅ ቃል አድርጌ ነበር።** አሁንም እንደዚያ ይመስለኛል። አንድ ትውልድ፥ ሁሉም አባላቱ ቢስማሙበትም ባይስማሙበትም፥

ሁሉም አባላቱ በእኩል ትጋትና ንቃት ተካፈሉበትም አልተካፈሉበትም፥ እድሜው በውል ላልተቆረጠ ለአንድ ዘመን እና ለነዋሪዎቹ፥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የጅምላ ባህርይ ሲሰጥ ይገኛል።

አንዳንዱ ዘመን ከጉልህ ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ሁኔታ ጋር የሚሄድ፥ የማይረሳ፥ በጎም ይሁን መጥፎ ስምና ተግባር ሊኖረው ይችላል። አንዳንዱ ደግሞ የተድበሰበሰ ቀለምና ገፅታ ይኖረዋል። ሁሉም ትውልድ ራሱን በራሱ የሚያይበት፤ ራሱን አብረውት ለኖሩ ሌሎች ሰዎች የሚያቀርብበት፤ በእርሱ ትውልድ ተፈፀሙ ስለሚባሉ ታዋቂ ድርጊቶች፥ በወቅቱ ላልነበሩ፥ ግን ዛሬ አብረውት ለሚኖሩ ሰዎች (በተለይ ለወጣቶች) የሚያቀርብበት፤ ወደፊት ለሚመጣ ትውልድ በፅሁፍ፥ በስነፅሁፍ፥ በሙዚቃ፥ በስእል፥ በቅርፃቅርፅ ወዘተ. ቀርፆ የሚተውበት መንገድ አለ። የአንድ ትውልድ ሀሳብ ገንኖ በሚነገርበት ዘመን የሚኖሩ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ስለዚያ ትውልድ የተለየ አስተያየት ሊኖራቸው ይችላል፤ ብዙ ጊዜ አላቸው። ባንድ ወቅት የተደነቀው በሌላ ጊዜ ወይ በምክንያት፥ ወይም ደግሞ በየሰበቡ ሊረገም ይችላል። ባንድ ወቅት በታላቅ ጩኸት የተወገዘው በሌላ ጊዜ በምክንያት ወይም ደግሞ በየሰበቡ ሊወደስ ይችላል። የታሪክ ጥናትም ቢሆን አስተያየቱን የሚመዝንበትና የሚያቀርብበት የራሱ ስርዓትና ቋንቋ ይኑረው እንጂ፥ ከዚህ ውጣ ውረድ ጨርሶ ሊፀዳ የሚችል አይመስልም። ዝርዝሩ ብዙ ያወያያል።

ዞሮ ዞሮ ግን፥ አንድ ነገር እውነት የሚሆን ይመስለኛል። **ያንድ ትውልድ ዋና መለዮ የዚያ ትውልድ አባላት፥ ከሞላ ጎደል በጅምላ የሚጋሩት አመለካከት እና አኗኗር ነው። የዚያ ትውልድ አባላት ግን በእድሜ ሊለያዩ ይችላሉ።** የእኔን ተመክሮ መነሻ አድርጌ ብናገር፥ በመሀከላቸው ያለው የእድሜ ልዩነት እስከ 25 ዓመት ሊደርስ እንደሚችል እገምታለሁ። ለምሳሌ፥ "የመሬት ላራሹ ትውልድ" ብለን ልንጠራው የምንችለው ትውልድ በኢትዮጵያ ውስጥ ገንኖ ወጥቶ የነበረ ይመስለኛል። የእርሱን ያህል ጠርቶ የወጣ፥ ስላንድ ጉዳይ ጮክ ብሎ አቅሙ በፈቀደለት መጠን በየአደባባዩ፥ ረዘም ላለ ጊዜ (እስከ 1967 ለማለት ይቻላል) የተሟገተ ቡድን፥ ከእርሱ በፊት በሀገሪቱ የነበረ አይመስለኝም። በዚያ ትውልድ አባላት መሀከል ያለው የእድሜ ልዩነት እስከ 25 ዓመት ሊዘልቅ ይችላል። እድሜው አንድ ዓመት የሆነና እድሜው 25 የሆነ ሰው በመሬት ላራሹ ውስጥ የተካተቱ፥ አንዳንድ ወይም ብዙ አመለካከቶችን ይጋሩ ነበር እንደማለት ነው። ለዚህ ይመስለኛል ያንድ ትውልድ አባል የሚባሉት። የእድሜንና የትውልድን ጉዳይ አቀልጥፎ ወይም አጉልቶ ለማሳየት ስል በዚህ መንገድ አቀረብኩት እንጂ የአንድ ዓመት ልጅ ስለ መሬት ላራሹ ያውቃል ለማለት አስቤ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። የትውልድ አንድነት የግድ የእድሜ ተመሳሳይነት ወይም

አንድነት ማለት እንደሚይመስለኝ ለማጉላት ነው የመሬት ላራሹን ሀሳብ የአንድ ዓመት ልጅና የ25 ዓመት ጎረምሳ እንደተጋሩት አድርጌ ያቀረብኩት። የ18 ዓመት ወጣትና የ42 ዓመት ጎልማሳ በወኔና በሚንተገተግ ስሜት ያስተጋቡታል ማለትም ይቻል ነበር። ወይም ሌላ...

## 2. የሚኒስቴር መ/ቤታችን ከቆመለት አላማ በመነሣት የመፅሄቱን ስያሜ "ትውልድ" ብሎታል፤ ይህ ስያሜ ይገልፀዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መጠሪያ ከተነሳን ስያሜው አንዳንድ ጥያቄዎች ሊያስነሳ ይችል ይመስለኛል። ምናልባትም፥ ይህ የኢንተርቪው ጥያቄ የቀረበውም ከዚህ ስያሜ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ጥያቄዎች ስለተነሱ ወይም ወደፊት ሊነሱ ይችላሉ ተብሎ ሊሆን ይችላል።

በሚኒስቴሩ ስም ውስጥ የተጠቀሰው አንድ የትውልድ ክፍል ብቻ ነው። እርሱም ወጣት ነው። ቀሪዎቹ ክፍሎች፥ ስፖርትና ባህል በቀጥታ አልተጠቀሱም። ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች "ትውልድ" የሚለው መጠሪያ የዛሬውን "ወጣት" ብቻ በማሰብ የተሰጠ ሊመስላቸው ይችላል። ባንፃሩ፥ "ስፖርትና ባህል እድሜን አይወስኑም። እኛ መጠንከር እያቃተን ይሆናል እንጂ በተለያዩ የእድሜ እርከኖች ላይ የምንገኝ ሰዎች የሚመጥነን አይነት ስፖርት ልንሰራም ሆነ ልንጫወት እንችላለን። ባህልም ያንድ ትውልድ ብቻ አይደለም። የሁሉም ነው። ስለዚህ፥ 'ትውልድ' የሚለው ስያሜ ሁሉንም ትውልድ የሚወክል ተደርጎ መታሰብ ነው ያለበት" የሚል መልስ ሊከተል ይችላል። እንዲህ እንዲህ ዓይነትና ሌሎች ጥያቄዎች ሊያስነሳ ይችል ይሆናል። ጥያቄው፥ ስያሜውን ከራሱ ከሚኒስቴሩ አሰያየምና አወቃቀር ጋር በማያያዝ የሚነሳ ሊሆን ይችላል ማለቴ ነው። ስም አውጪዎቹም፥ በእንዲህ ዓይነቱ መስሪያ ቤት የሚወጣን መፅሔት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚጠራ ስም ሲፈልጉ ካጋጠማቸው ችግር ይመስላል እዚህ ላይ ያረፉት። ይህ ሁሉ መላ-ምት ነው።

በጥያቄው መሰረት፥ ስያሜውን ሚንስቴሩ ከቆመለት ዓላማ ጋር አያይዤ፥ "ዓላማውን ይገልፃል አይገልፅም?" ለማለት ስሞክር በጣም ተቸግሬያለሁ። ወደሰነድ ምርመራም አምርቻለሁ። ነሐሴ 1987 በወጣው ሕገ መንግስት (አዋጅ ቁጥር 1-1987) ውስጥ እና በአዋጅ ቁጥር 4-1987 ውስጥ በተጠቀሱት የባህል መብቶች፥ በባህል ነክ

ዓላማዎች እና የሚንስቴሩ ስልጣንና ተግባራት ውስጥ በጣም ጎልተው የወጡት ባህል፥ ልማድ፥ የተፈጥሮ ሀብት፥ የታሪክ ቅርስ፥ ኪነጥበብ፥ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ናቸው።

ጥር 1990 በተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀው የባህል ፖሊሲ ሌላ ሚኒስቴሩ ስለቆመበት ዓላማ በቅርቡ ወጥቶ ያነበብኩት ሰነድ የለም። በጥያቄው መሰረት፥ እውስጡ የተጠቀሱትን ዘጠኝ ዓላማዎች እንደገና ስመለከት እነርሱም ያተኮሩት፥ ከሞላ ጎደል ከፍ ብዬ በጠቀስኳቸው ጉዳዮች ላይ ነው። ይህንን ሁሉ ይዤ፥ አስተያየቴን ልስጥ።

እኔም የሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ስያሜ ከሚጠቀማቸው ነገሮች ልነሳ። ይህ ሚኒስቴር "የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር" በመባል ጀምሮ፥ "ማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር" ተብሎ፤ አሁን ደግሞ "የወጣቶች፥ የስፖርትና የባህል ሚኒስቴር" ተመባል ደርሷል። በስያሜዎቹ ውስጥ ሁሉ "ባህል" ሁለተኛና ሶስተኛ ቦታ ይዞ የተገኘው ያለምክንያት አይደለም። (በዚህ ላይ ያለኝን ሃሳብ እዚህ ለማቅረብ ጥያቄው አይፈቅድልኝም።) ባሁኑ ስያሜ ውስጥ **ወጣቶች** ቀዳሚውን ስፍራ ይዟል። ባሁኑ ጊዜም የወጣት ጉዳይ ትኩረት እየሳበ ስለሚመስል፥ የመፅሔቱ ርእስ "ትውልድ" የተባለውም ይህንን ትኩረት ለማንፀባረቅ መስሎኛል። ይህ መፅሔት የመስሪያ ቤቱ ዋናና ብቸኛ መፅሔት ከሆነ፥ ስያሜው ከሚኒስቴሩ ዓላማና ተግባር ጋር ተሰናኝቷል ለማለት ያስቸግረኛል።

እርግጥ፥ ይህ አለመሰናኘት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተም አይደለም። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ "የማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር" ይባል በነበረበት ጊዜ የወጣ "ባህል" የሚባል (በጊዜው "አንድ ለእናቱ" እንዳይሆን ሰግቼለት የነበር) መፅሔት ውስጥም የታየ ነበረ። በ1988 የወጣውን መፅሔት ስመለከት (ከእርሱ ሌላ የወጣ አይመስለኝም) በአዋጆችና በ1990 በወጣው ፖሊሲ ውስጥ የተዘረዘሩትን ርእሰ ነገሮች በጣም የሚያካትት ዓይነት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ብዙዎቹ ርእሰ ነገሮች ደግሞ ባህል-ነክ ነበሩ። ስለዚህም የመፅሔቱ መጠሪያ ከሚንስቴሩ ዓላማና ተግባር መሀል ባህልን ከሚመለከተው ጋር ብቻ ነበር የተሰናኘው። ምክንያቱም፥ በመጠሪያው ውስጥ ቀድሞ ስለሰፈረው "የማስታወቂያ" ጉዳይ፥ በ1987 በወጣው አዋጅ ውስጥ የተጠቀሰውን ስልጣንና ተግባር መሰረት አድርጎ የወጣ ምንም ፅሁፍ አልነበረም። ይህ መቼም ስለአጠቃላይ አሰራራችን የሚናገረው አያጣም። ምናልባት፥ "ባህል" በተባለው መፅሔት ውስጥ ባህል-ነክ ይዘት የገነነው በዝግጅቱ ውስጥ የተሳተፉት የባህል ሰዎች ወይም አፍቃሬ ባህሎች ስለሆኑ ይሆናል። ዛሬስ?

## 3. የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለያዩ የፖለቲካ፥ የማኀበራዊና የኢኮኖሚ ስርዓቶች ውስጥ አልፈዋል። በነዚህ ሂደቶች ውስጥ የትውልዶችን ሚና እንዴት መግለፅ ይቻላል? ያለፈውንና ያሁኑን ትውልድ በማነፃፀር አንድነትና ልዩነቱን ማመልከት ይቻላል?

በእኔ አስተያየት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ከፍ ተብሎ እንደተገለፀው በተለያዩ የፖለቲካ፥ የማኀበራዊና የኢኮኖሚ ስርዓቶች ውስጥ አልፏልም፥ አላለፈምም ብሎ መናገር ይቻላል። ምርጫችንን የሚወስነው የቆምንበት ቦታ ነው። እርግጥ፥ የተለያዩ መንግስታት ከቆሙበት ቦታ ቆሞ የሚናገር እንደነርሱ "አልፏል" የሚል ይመስለኛል። እኔ ግን አልልም። ምክንያቱም፥ ብዙ ጊዜ የሀገራችን መንግስታት ባወጧቸው ድንጋጌዎች፥ ለሕዝብ በአዋጅ ሰጠን በሚሏቸው መብቶችና፥ ባሰፈሯቸው አስጎምጂ የኢኮኖሚ እቅዶች ሲፍለቀለቁ በእኔ እድሜ የታዘብኩ ስለሚመስለኝ ነው። "ሕዝብ"፥ ወይም የተሻለ የማውቀው "እኔ እራሴ"፥ ከቆመበት ቦታ ሆኖ የሚናገር ደግሞ፥ "አልፌያለሁ"ም "አላለፍኩም"ም የሚል ይመስለኛል። ጥቂት ላፍታታው ልሞክር።

ከራስ ተፈሪ ዘመን ተነስተን፥ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን በኩል ወደዘመነ ደርግ እና ወደያዝነው ዘመን ስንመጣ፤ በየዘመኑ የፖለቲካ፥ የማኀበራዊና የኢኮኖሚ አዋጆችና ደንቦች ሲወጡ እናያለን። ከዱሮው ወደዛሬው ስንመጣም እነዚህ አዋጆችና መመሪያዎች በገፍ-በገፍ ሲወጡ እንመለከታለን። ይህ ማለት ግን ሕዝቡ በተለያዩ ስርዓቶች ውስጥ ኖሯል፥ <u>በተለያዩ ስርዓቶች ውስጥ አልፏል ማለት አይደለም</u>። ምክንያቱም <u>በተለያዩ ስርዓቶች ውስጥ አልፏል ማለት</u> ውስጥ፥ "በአዋጆቹና በመመሪያዎቹ ላይ የሰፈሩት ሀሳቦች በስራ ላይ ውለው፥ የሕዝቡን አኗኗር፥ ትርጉም ባለው መንገድ ለውጠዋል" የሚል አንድምታ አለ። <u>በተለያዩ አዋጆች፥ ሕጎችና መመሪያዎች ውስጥ አልፏል ማለት ሳይሻል ይቀራል?</u> ሲያልፍም ብዙ ጊዜ የጎሪጥ እየተያየ፥ አንዳንዴ እያደናቀፉት፥ አንዳንድ ጊዜ እየተራመዳቸው፥ አንዳንዴ ለመኖር ሲል እያባበላቸው፥ አንዳንዴ እነሱ እየረገጡና እያሹት ይመስለኛል። ባጭሩ፥ የተከባብሮና የተጣጣሞ ጉዞ ሳይሆን የተሸነጋገሉና የድብብቆሽ ኑሮ መስሎ ነው የሚሰማኝ። ስለዚህ፥ አዋጆቹ፥ ሕጎቹ፥ ፖሊሲዎቹ እና መመሪያዎቹ በሕዝቡ ውስጥ ያለፉ መስሎ አይሰማኝም። ይህንን አስተያየት ሶስቱም መንግስታት የሚቀበሉት አይመስለኝም። ይሁንና "አልፏልም! አላለፈምም!" ማለት ይቻላል ያልኩት ለዚህ ነው።

አንድ የገበሬ ገጣሚ ባንድ ወቅት የገጠመው፥ ይህንን የተደፋፍጦ ኑሮ በይበልጥ ፍንትው አድርጎ ስለሚገልፀው የእርሱን ግጥም መጥቀስ ጠቃሚ ነው። የሚናገረው፥ ስለእርሱና ስለሹማምንት አኗኗር ነው። እንዲህ ነበር ያለው፤

**ድመት እጎታ ላይ፥ አይጥ ተጎታ ስር፥**
**ድመት እይዝ እይዝ፥ አይጥ አመልጥ አመልጥ፥**
**እንደዚያ ያለ ነው፥ የእኛ አቀማመጥ።**

ይህንን ካልኩ በኋላ ስለትውልዶች ልናገር የምችለው ውስብስብ ነው የሚሆነው። ከፍተኛ ባለስልጣናት በየዘመኑ በሚናገሩትና ብዙሃኑ ሕዝብ በሚኖረው ኑሮም ውስጥ የሰምና ወርቅ ጨዋታ አለበት። ያንን በዝርዝር ለማስተንተን ቦታውም ጊዜውም የለም። ስለዚህ ከዚህ በላይ፥ ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሆን በማለት የሰጠሁትን አጠቃላይ አስተያየት በዚሁ ዘግቼ፥ ስለትውልዶች ሁኔታ የተጠየቀውን ደግሞ ራሱን እንደቻለ ጥያቄ ቆጥሬ አስተያየቴን እሰጣለሁ። ታድያ፥ ትኩረቴን የእኔ በሚመስለኝ ትውልድ ላይ እንዳደርግ እገደዳለሁ። በመጠኑም ቢሆን ላውቅ የምችለው እሱን ነውና።

በ1940ዎቹ መጀመሪያ ገደማ ተወልደን፥ ዛሬ በ50ዎቹ የእድሜ ክልል የምንገኝ ሰዎች አፍላውን እድሜያችንን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የኖርን፤ የጉልምስናችንን የመጀመሪያ ግማሽ፥ በዘመነ ደርግ ከትዝብት ጋር መሬት ለመሬት የጎተትን፤ ሁለተኛውን ግማሽ ደግሞ በዘመነ "ኢህአዴግ" የምንጎትት ይመስለኛል። ሁሉንም ወክዬ ከምናገር መጀመሪያ ስለእኔ፥ ስለሰፈር እና ስለ ትምህርት ቤት ጓደኞቼ ብቻ የማውቀውን ያህል ላውጋ። ከዚያ ስለዘመነ ደርግ እና ስለዛሬ ያስተዋልኩትን እናገራለሁ።

እኔ የተወለድኩት፥ በ1941/1942 አዲስ አበባ፥ የጥንቱ ሽሮ ሜዳ፥ ዛሬ የስርዓተ ትምህርት ሕንፃ እተገነባበት አካባቢ ነው። ያደግሁት "ዶርዜ ሰፈር" በመባል ይታወቅ በነበረው በኃይለመለኮት መንገድ ባለው ሰፈር ነው። የሽሮ ሜዳ እና የመነን ልጅ ነኝ ማለት ነው። የተማርኩት ከ3-12 ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ሲሆን ከዚያ በኋላ ደግሞ በቀኃሥ ዩኒቨርሲቲ ነው። እኔና ጓደኞቼ፥ ከፋም ለማም፤ በቤተሰብ፥ በትምህርት ቤትና በማኀበረሰብ ምክርና ቁጥጥር ያደግን ይመስለኛል። በየሄድንበት እነዚህ ሶስት አካላት የምንሰራውን በጎ ነገርና ጥፋት የሚያዩ እየመሰለን በተቻለ መጠን ላለማጥፋት እየተጠነቀቅን የኖርን ይመስለኛል። ባጭሩ፥ የእነሱ ነበርን ማለት ይቻላል።

በዘመነ ደርግ ይህ ሁኔታ የተናጋ ይመስለኛል፡፡ ብዙው ነገር ከንብረት መወረስ ጋር የተወረሰና የመንግስት የሆነ ይመስላል፡፡ አኢወማ (የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኀበር) እና አኢሴማ (የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማኀበር) ከተቋቋሙ በኋላማ የልጆች ነገር እየለየለት ሄደ፡፡ ሴቷ ልጅ አኢሴማ ብላ ስትሄድ ቤተሰብ ሊከለክል አይደፍርም፥ "ፀረ-አብዮት" መባል አለና፡፡ የፀረ-አብዮትነት መዘዙ ደግሞ ብዙ ነው፡፡ ወንድ ልጁ አኢወማ ብሎ ሲወጣ ቤተሰብ አሁንም አይቆጣጠርም፡፡ በተለይ በአኢሴማና በአኢወማ ስም ልጆች ከቤተሰብ ቁጥጥር ገና በለጋነታቸው የወጡ ይመስለኛል፡፡ ልጅ ከቤተሰብ ተነጠቀ፡፡ ነጣቂውም ሜዳ ላይ የጣለው እንጂ በስርዓትና በወግ ያሳደገው አይመስለኝም፡፡ ትምህርት ቤቱም የተጋጋለ የቡትልክና መድረክ ስለነበረ ስነምግባርን ተቁምነገር ቆጥሮ አላስተማረውም፡፡ እንዲያውም፥ ባንድ በኩል እንደልቡ ያፍሰው፥ ያፍነው፥ ያሳድደው እና ያሰድደው ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መረን እንዲሄድ ያደርግ ነበር፡፡ ባጭሩ፥ ልጅ የመንግስት ሆነ፡፡ ቤተሰብ፥ ማኀበረሰብና ትምህርት ቤት ፊት የነበራቸውን ሚና አጡ፡፡

ባለፉት 12 ዓመታት ደግሞ፥ ሁሉም ባለቤት አጡ፡፡ ሁሉም የየራሳቸው ባለቤት ሆኑ፡፡ ወጣቱ፥ ጎልማሳውና ኮረዳዪቱ፥ አዛውንቱና እናቶች፤ ሬድዮው፥ ቲቪው፥ ቪድዮው፤ ቤተሰቡ፥ መንደሩ፥ ቀበሌው፥ ማኀበረሰቡ፥ ትምህርት ቤቱ፤ በጠቅላላው ሀገሩ፤ ያለጥናትና ያለመመካከር በቅፅበት ተበረገዱ፡፡ ምናልባት የተዘጉትን ያህል የተበረገዱ መሰሉ ማለት ይቻላል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት መኖሩ አያጠራጥርም፡፡ አሁን ያንን ማስተንተን አይቻልም፡፡ አንድ ነጥብ ግን ግልፅ ይመስላል፡፡ እርሱም፥ የምር የምንወያይባቸው የስነምግባር፥ አንዳንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታዎች፥ የከተማ ፅዳት፥ ሙስና፥ እና የኑሯችን ነገር ሁሉ በዚህ አውድ (context) ውስጥ የሚታዩ መሆናቸው ነው፡፡ ባጭሩ፥ <u>**በጥቅሉ**</u> ስመለከተው፥ ወጣቱ ባለቤት አጣ ነው የምል፡፡ በሶስቱ መንግስታት፥ ልጁ በተለያዩ ወገኖች እጅ ወድቋል ነው የምል፡፡ ማኀበረሰቡ የተረጋጋና ተለጣጣቂነት ያለው ሕይወት ስለሌለው ሁሌ የተጠንቀቅና የጥርጣሬ ኑሮ ስለሚወቅጠው ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፈውም ይኸው የድፍጫ ኑሮ ይመስለኛል፡፡ በአፄው ዘመን የቤተሰቡ፥ የትምህርት ቤቱና የማኀበረሰቡ የነበረው ወጣትም፤ በደርግ ዘመን በግዱ የደርግ፥ በኢህአዴግ ዘመን ደግሞ የራሱ ሆነ፡፡ ከመንግስት መንግስት ሲተላለፍ እያልበጀው ሄደ፡፡ የትውልዶች እጣ ፈንታም እንዲህ ዓይነቱን የኑሮ ፍልስፍናና አኗኗር መሰረት አድርጎ የተገነባ ከመሰለኝ ውሎ አድሯል፡፡

ከዚህ በላይ ባሉት አራት አንቀፆች ያሰፈርኳቸው ወዳድል ሀሳቦች ብዙ ፈተና እንዳለባቸው አምናለሁ። ጉዳዩ፥ በስፋትና በጥልቀት ምርምር ሊኪያሄድበት የሚገባ፥ የብዙ ባለሙያዎችንም እውቀትና ትጋት የሚሻ መሆኑ ጥርጥር የለውም። እስከዚያው ግን ሁላችንም ያስተዋልነውን መጋራታችን ይጠቅማል በሚል እምነት ነው የእኔን አስተያየት ሳልታቀብ ባጭሩና በጥቅሉ መሰንዘሬ። ዝርዝር ውስጥ ከገባን ብዙ ነገር አለ። በእንዲህ ዓይነቱ ኢንተርቪው ያንን ማድረግ እንደማይቻል ግልፅ ነው።

## 4. የወጣቶች፥ ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር ርእይ "የተሟላ ሰብእና ያለው፥ ኢትዮጵያን ከድህነት በማላቀቅ ወደ ብልፅግናና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያሸጋግር ወጣት ትውልድ ተፈጥሮ ማየት" ይላል። ይህን ርእይ እውን ለማድረግ ይህ ትውልድ ካለፈው ትውልድ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ምን ይማራል?

በመጀመሪያ፥ በዚህ ጥያቄ ውስጥ ያስተዋልኩትን፥ የቋንቋ አጠቃቀም ብዙ ጊዜ ይፋ የሚያደርገውን፥ እኛ ግን ተቁምነገር የማንጥፈውን አንድ ነጥብ ላንሳ። ጉዳዩ "ተፈጥሮ ማየት" ከሚለው ሐረግ ጋር የተያያዘ ነው። የተባለውን ትውልድ ማን ነው የሚፈጥረው? የተፈጠረውንስ ማን ነው የሚያየው? ይህ ርእይ በጥሞና ታስቦበታል?... አሁን ወደጥያቄው ላቅና። ካለፈው ትውልድ ምን ይማራል በተባለው ልጀምር።

**አንደኛ፥** ካለፈው ትውልድ ትግል ሊማር ይችላል ብዬ አስባለሁ። ሊማር የሚገባውም ከአዎንታዊውም ከአሉታዊውም ልምድ ነው። አብዛኛው የ1950ዎቹ የመጨረሻ አጋማሽና የ1960ዎቹ ወጣት ትውልድ፥ ሀገሪቱ ከድኅነት እንድትላቀቅ፥ ፍትሕና ርትእ እንዲሰፍኑባት፥ በልማት ከሌሎች የዓለም ሕዝቦችና ሀገሮች ጋር እንድትስተካከል ለመታገል ቆርጦ የተነሳ ትንታግ ትውልድ የነበር ይመስለኛል። አብዛኛው የዚህ ትውልድ አባል ለሕይወቱ ምንም ያልሳሳ፥ ከግል ኑሮው ይልቅ ለማኅበረሰባዊ ደኅንነት ሲያስብና ሲያሰላስል የኖረና የሞተ ትውልድም ይመስለኛል። የዛሬውም ሆነ መጪው ትውልድ መማር ከሚችላቸው ቁምነገሮች መሀል ቆራጥነቱና ከራሱ ይልቅ ላስተማረው ደኃ ሕዝብ አብልጦ ማሰቡና መታገሉ ጎልተው የሚታዩ ይመስለኛል። እነዚህን ጥቂት አቃንቶ ሊወርሳቸው ይችላል፥ በእኔ እምነት ደግሞ ሊወርሳቸው ይገባል።

**ሁለተኛ፥** በእኔ ግምት፥ ከዚያ ትውልድ፥ ከአስር ውስጥ ዘጠኝ ተኩል እጁ፥ ሊለውጠው ስላሰበው ነገር የነበረው እውቀት ልክ እና፥ የፍላጎት-የጉጉቱ ልክ የተመጣጠኑ አለመነበራቸው ነው:: ፍላጎትና ጉጉቱ ከእውቀቱ በልጠው የተትረፈረፉ የነበሩ ይመስለኛል:: የሚያሳዝነው፥ ይህ ሁኔታ ከዚያ በኋላ እየባሰበትና እየከፋ መሄዱ ነው:: ለምሳሌ፥ የመደብ ትግል ሊያኪያሄድ ቆርጦ የተነሳው ትውልድ በሀገሪቱ ውስጥ ስላለው የመደብ መዋቅር አስተማማኝ መረጃ ከብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ሰብስቦ፥ ያንን ተንትኖ አውቆ፥ በትንተናው መሰረት የትግል ስልት ነድፎ፥ እውቀቱንና ስልቱን ለትግሉ አካላት በተለያዩ መንገዶች አሰራጭቶ፥ ነገሮችን አብላልቶ፥ በዚያ መሰረት የተንቀሳቀሰ አይመስለኝም:: ስርነቀል የመሬት ስሪት ለውጥ ለማምጣት ሊታገል ቆርጦ የተነሳ ትውልድ፥ የሀገሪቱ የመሬት ስሪት በመላ ሀገሪቱ ምን-ምን ይመስል እንደነበር በወቅቱ ያውቅ ነበር ብዬ አላስብም:: እንኳን ያኔ፥ ዛሬም ቢሆን በየቦታው ያለው የመሬት አያያዝና አጠቃቀም፥ ከዚያም ስሪት ጋር የተያያዘው የሰዎች የተለያየ አመለካከትና አኗኗር፤ በየአካባቢያቸው ሰዎች ምን እንዲደረግ፥ ምን እንዳይደረግ እንደሚፈልጉ፤ ለውጥ ይፈልጉ እንደሆነም ምን ዓይነት ለውጥ እንደሚፈልጉ፥ በምን በምን ጉዳይ ላይ ለውጥ እንደሚፈልጉ በትክክል የሚታወቅ አይመስለኝም:: የ1966 አብዮት በድንገት መምጣትም፥ በጥቅል እውቀቶችና ግምቶች፥ ባልታሰበ ፍጥነት እና በወጉ ባልተመጠነ አደረጃጀት ብዙውን ነገር የመወሰንን እና የማከናወንን ልማድ አስፋፍቶታል:: ከዚህም ወጣቱ የሚማረው ብዙ ቁምነገር ያለ ይመስለኛል::

**ሶስተኛ፥** የሀገሪቱ የትምህርትና የፖለቲካ አኪያሄድ፥ በተለያዩ ዘመነ መንግስታት ከተለያዩ ሀገሮች በተወሰዱ ርእዮተዓለሞች ሲወዛወዝ ቆይቷል:: እስከዛሬ፥ ያፈራው ፍሬ፥ እየተባባሰ የሄደ ድኅነት ብቻ ነው:: ይህ ሁኔታ፥ የዛሬውና የመጪው ትውልድ ከራሱ ኢኮኖሚያዊ፥ ፖለቲካዊ፥ ባህላዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች የሚመነጩትን የሀገር ውስጥ ፕሮብሌሞች በተቻለ መጠን በራሱ መንገድ መፍታትን እንደቀዳሚ ተግባር ቆጥሮ፥ በዚያ መሰረት እንዲያስብ፥ እንዲያቅድና እንዲተገብር ሳይመክረው ይቀራል?

ዛሬ በሕይወት ያሉ የዚያ ትውልድ "ርዝራዦች" ደግሞ፥ ዛሬ እንደበፊቱ ባጭርና ቅልብጭ ባሉ ቅዕሎች የሚገለፁ ሳይሆኑ በሌሎች፥ በብዙ ዓይነት ውስብስብና ተደራራቢ ቅዕሎች የሚገለፁ ከመሆናቸውም፥ ልዩ ትምህርት የሚያገኝ ይመስለኛል::

ለማንኛውም፥ ይህ ሁሉ ትምህርት የሚገኘው አንድም፥ የትውልዱ ታሪክ በተቻለ መጠን፥ ወገናዊነት ባልተጠናወተው አካዳሚያዊ ትጋት፥ በስፋትና በጥልቀት ሲጠና ነው:: አንድም ደግሞ፥ በትግሉ ተሳታፊ የነበሩት በሙሉ፥ በተለይ ደግሞ አውራ-አውራ የሆኑትና በከፍተኛ የፖለቲካ ውሳኔዎችና ክንዋኔዎች ውስጥ ተሳትፈው የነበሩት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ሳያፍሩ፥ ሳይፈሩ፥ ሳይወላውሉ፥ በድርጅት ወገናዊነት አሳባቸውን ሳይጋርዱ፥ በየግላቸው፥ መልስ የፃፉ እንደሆን ወይም በየአደባባዩ የተናገሩ እንደሆን ነው:: እያንዳንዳቸው ሊመለከቷቸው ይገባል የምላቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፤ "**መጀመሪያ፥ ወደ ተማሪ ንቅናቄ እንዴት ገባሁ? ለምንስ ገባሁ? ስገባ ስለጉዳዩ የነበረኝ እውቀት ምን ዓይነት ነበር? ወደ ድርጅት ፖለቲካ ለምንና እንዴት ገባሁ? ስገባ ምን አደርጋለሁ ብዬ ነበር የገባሁት? ስለፖለቲካ ድርጅት የነበረኝ እውቀት ምን ነበር? ከገባሁ በኋላ ምን-ምን ተናገርሁ? ምን-ምንስ በተግባር ፈፀምሁ? ዛሬ በምን ሁኔታና ኑሮ ላይ እገኛለሁ? የሆነውን ሁሉ ወደኋላ በምናብ ጉዞዬ ስቃኘው እና ስመዝነው ምን ይሰማኛል? ከዚህ ሀሳብና ስሜት ተነስቼ ለዛሬውና ለመጪው ትውልድ ምን ምክር ላስተላልፍ?...**" እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እያነሳን በሬድዮና በቴሌቪዥን ጭምር ፍርጥርጥ አድርገን ካልተወያየን ለዛሬው ትውልድ ፋይዳ ያለው ትምህርት እንስጣለን ብሎ ማሰብ የሚቻል አይመስለኝም:: እስከዚያው፥ እኔም ሆንኩ ሌላው ሰው የሚሰጠው ሀሳብ ከተለመደው ተደጋጋሚና አሰልች አስተያየት የሚያልፍ አይመስለኝም:: እርግጥ፥ እሱም ቢሆን ማዝገሚያ ሆኖ ማገልገሉ አይቀርም፤ እያገለገለም ነው::

ሌላው የዚህ ጥያቄ አቢይ ክፍል፥ "የተሟላ ሰብእና ያለው ወጣት"ን የ"መፍጠር" ጉዳይ ነው:: የተሟላ ሰብእና ያለውን ዜጋ ማፍራት የሚቻለው በቤተሰብ፥ በትምህርት ቤቶች፥ በማኅበረሰብ፥ የህፃናትንና የወጣቶችን ጉዳይ ስራዬ ብለው በያዙ የመንግስትና የግል ድርጅቶች፥ በመገናኛ ብዙኃን፥ በሃይማኖት ድርጅቶች እና፥ ልምድና እውቀት ባካበቱ ግለሰቦች የጋራ፥ የተሰናሰለ (በሰንሰለት መልክ በተያያዘ) እና የተደጋገፈ ጥረት ብቻ ነው:: በዚህ መሰረታዊ ሀሳብ ላይ ለመነሻ ያህል መግባባት ከተቻለ፥ ቀሪው የአተገባበር ስልትና ፕሮግራም ሊከተል ይችላል:: እርሱ ደግሞ በእንዲህ ዓይነቱ ኢንተርቪው የሚዘረዘር አይደለም::

እስከዚያው ግን፥ "የተሟላ ሰብእና ያለው መልካም ዜጋ" ምን ዓይነት ነው ብዬ እንደማስብ ካንድ ሌላ ፅሁፌ እንድጠቅስ ይፈቀድልኝ:: ይህንን የማደርገው፥ ሀሳቤን ከአንባብያን፥ በተለይ በግለሰብ ደረጃ ከሚፍጨረጨረው የወጣት ክፍል ጋር፥

ለመጋራትና ምን-ምን ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባው በስሱ ለመጠቆም ስል ብቻ ነው።

የተሟላ ሰብእና ያለው መልካም ዜጋ፡-

> **ጥሩ ምግባር ያለው[1]፥ ራሱንና ሌሎች ሰዎችን የሚያከብር፥ ፈሪኀ ኀሊና ያለው፥ በነፃና በእውቀታዊ አስተሳሰብና አሰራር የሚያምንና ይህንኑ የሚተገብር፤ ስለሀገሩና ስለህዝቡ የሚያውቅና ስለሁለቱ ደኅንነት እና ልማት የሚቆረቆርና ለስራ የሚተጋ፤ ማንኛውንም ዓይነት ጭቆና የማይቀበልና እንዲወገድም የሚታገል፤ በአእምሮው ሀገራዊውን፥ አኀጉራዊውን እና ዓለማቀፋዊውን እየመዘነ ለራሱ፥ ለሀገሩ ህዝብ እና ለሰውልጅ በጠቅላላ የሚበጀውን የሚያስብ፥ የሚጨነቅና ሀሳቡንም አቅሙ በፈቀደ መጠን ተግባራዊ የሚያደርግ፤ መናገር ብቻ ሳይሆን ማድመጥም፥ ሌሎች እንዲችሉት የሚሻ ብቻ ሳይሆን እርሱም ሌሎችን የሚችል (ባጭሩ፥ በመቻቻል የሕይወት መርህ የሚያምን)፤ ተፈጥሮን ማጥናት፥ ማወቅ፥ ማድነቅ፥ መጠበቅና ማልማት የሚችል፤ ልዩልዩ ጥበባትን (ስነፅሁፍ፥ ሙዚቃ፥ ፊልም፥ ስእልና የመሳሰሉትን) መመልከት፥ ማንበብ፥ ማድነቅ እና መረዳት የሚችል፤ ወዘተ. ነው። ዝርዝሩ አያልቅም። ባጭሩ ግን፥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ "ካልቸርድ ፐርስን" (cultured person) የሚባለውን ነው እኔ መልካሙ ኢትዮጵያዊ ዜጋ እንዲሆንልኝ የምመኘው። መቼም ይሄ ህልም ነው። ህልም ደግሞ በዓለም ላይ ገና አልተከለከለም።**

እንዲህ ዓይነቱ ዜጋ ከራሱ አልፎ፥ ለሀገሩና ለሰውልጅ (humanity) ይተርፋል ብዬ አምናለሁ። የወጣቶች፥ የስፖርትና የባህል ሚኒስቴርም እንዲህ ዓይነቱን ዜጋ ለማፍራት እንዲጥር እመክራለሁ።

## 5. ባህል ለኢትዮጵያ ህዝብ ልማትና አንድነት የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው ብለው ያምናሉ? የወደፊቱስ አቅጣጫ ምን መምሠል አለበት? ወጣቱስ ምን ይጠበቅበታል?

---

[1] ይህንን "ያለው/ያላት" እያልኩ መፃፍ ጀመርኩና አንባብያንን እና እኔን እንደሚያስቸግር ስገነዘብ ተውኩት። "መልካም ዜጋ" ስል የማስበው ስለሁሉም ፆታዎች መሆኑን ለአንባብያን በትኅትና መግለፁ ይበቃል ብዬ አምናለሁ።

ይህ ጥያቄ አንድ ይምሰል እንጂ ቢያንስ አራት ነው:: **ባህል ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው ብለህ** ታምናለህ በሚለው ልጀምር::

በተለያዩ ዘመናት፥ ኢትዮጵያ በሚባል ስም ስትጠራ ተዛሬ ለደረሰችው ሀገራችን አንድነት ሲሉ፥ አነሰም በዛም፥ ነገስታትዋና መሪዎቿ የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ሳያደርጉ አልቀሩም:: ባንፃሩ፥ በሀገሪቱ ሕዝብ የአኗኗር ስልት ውስጥ በዝምታ የተሰራ የተገነባ፥ የታነፀ ልዩ ባህርይ ያለው የአንድነት ዓይነትም ያለ ይመስለኛል:: እንዲያውም ዋናውና መድኅናችን ሆኖ የቆየው እርሱ ይመስለኛል:: ቃሉ ያው "አንድነት" ይሁን እንጂ፥ በየዘመኑ የተለያየ ፍች የነበረው ይመስለኛል:: ዛሬም እንዲሁ የራሱ ትርጉም ያለው ይመስለኛል:: ለምሳሌ፥ በአምስቱ የጣሊያን ወረራ ዘመናትና ከ1933 በኋላ ለተወሰኑ ዓመታት ቃሉ የነበረው ፍች አንድ አይመስሉኝም:: ወዲህ፥ ለእኛ ወደሚቀርበን ዘመን ስንመጣም፥ በ1983 የነበረው የአንድነት ፍች እና ዛሬ ያለው የአንድነት ፍች እንኳ ለሁላችንም ተመሳሳይ ናቸው ብዬ በግሌ አልገምትም:: ይህንን የምለው ታድያ፥ የቃሉን ተራ ትርጉም፥ "አብሮ መሆን" የሚለውን ለመጥቀስ ሳይሆን በየዘመኑ በሀገሪቱ ጉሉሃን (elites) በአደባባይ የሚነገረውን፥ የሚፃፈውን እና የሚደረገውን ለመጥቀፅ ነው:: ለጊዜው፥ የጥያቄው ፍላጎት ወደዚህ ዓይነት ጉዳይ ያነጣጠረ አይመስልም:: ነጥቡ፥ በጅምላ፥ ባህል ለአንድነት ምን አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል ዓይነት ነው:: ከፍ ብዬ ትንሽ እንደቃጣሁት፥ ጥያቄውን መልሶ መጠየቅም ይሁን መልሱን አጥርቶ መመለስ እንዲህ በቀላሉ የሚወጧቸው ተግባራት አይደሉም:: ውስብስብ ጉዳዮች ውስጥ የሚያስገቡ ይመስለኛል:: እኔ ግን ላይ ላዩን ብቻ ልመልስ::

በእኔ አስተያየት፥ ዛሬ አብረን ባለንበት መልክ እንድንኖር ከማንም በላይ አስተዋፅኦ ያደረገው ባህል ወይም የአኗኗራችን ስርዓት ነው :: ብዙው ኑሯችን ደግሞ፥ በሂደት እራሱን እየሰራ የሄደና እየሄደም ያለ እንጂ ሰዎች ሆነ ብለው፥ ከዓለማዊ ትምህርትና እውቀት የሚመነጭ ስርዓትን በአዋጅና በመግለጫ እያስረዱና እየገደቡ አድቦልቡለው የቀረፁት አይመስለኝም:: ከሶስት ዓመት በፊት ያልኩትን፥ ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሆንልኝ እንዳለ ባሰፍረው ይቀለኛል:: ምክንያቱም በዚያ ላይ የምጨምረው አዲስ መረጃም ሆነ አስተያየት ዛሬ የለኝም:: እንዲህ ነበር ሃሳቤን ያሰፈርኩት::

"ሁላችንም እንደምናውቀው ኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ልዩ ልዩ ጎሳዎች (ብሔረሰቦች) የሚገኙባት ሀገር ነች። ለአነጋገር እንዲያመችም፥ ቢያንስ በሶስት ሊመደቡ የሚችሉ ታላላቅ ሀይማኖቶችም ያሉባት ሀገር ነች ማለት ይቻላል። ሀገር-በቀል ሃይማኖቶች፥ ክርስትና እና እስልምና ለረዥም ዘመናት አብረው የቆዩባት ሃይማኖቶች መሆናቸውም የታወቀ ነው። ምናልባት ለሁላችንም ግልፅ ሆኖ ገና ያልታየ፥ ስለዚህም ስለኢትዮጵያ ስንናገርም ሆነ ስንነጋገር፣ መሪዎች፥ ተርታ ግለሰቦች፥ ወይም ምሁራን ሆነን ስናወሳው የማንደመጠው አንድ ሊታሰብበት የሚገባ ቁምነገር ያለ ይመስለኛል። ይኸውም በሰላምና በጦርነት፥ በጠብና በፍቅር፥ በመጋደልና በመተሳሰብ መሀል ከነዚህ ሶስት ሃይማኖቶች የበቀለ ያኗኗር ዘይቤ ነው። እኛ፥ 'ማን የኢትዮጵያን ድንበር ከባህር ማዶ ድረስ ሳይቀር አሰፋ? ማን ማንን አስገበረ? ማን የማንን መሬት ነጠቀ? ማን የማንን ሕዝብ ጨፈጨፈ? ማን ምን አስገበረ? ማን የመሳፍንቱን ሀገሮች አንድ አደረገ? ማን የኢትዮጵያን አስተዳደር ስርዓት አስያዘ? ወዘተ.' እያልን ታሪካዊ ምርምርና ጥናት እያደረግን ያንን ስናስተጋባ፣ በጦርነትና በንግድ ለብዙ ዘመናት እየተገናኘ ያለው ሕዝብ ድምፁ ሳይሰማ፣ በሰላሙ ጊዜ ባንድ በኩል ተጓዡ ነጋዴ አገር አቋርጦ ሲነግድ፥ እነገደበት ቦታ አብሮ ሲበላ ሲጠጣ፥ እነገደበት ቦታ ሲያድር፥ ሲተቃቀፍ፥ ሲዋለድ፥ እንደ ዘበት ዲቃላ ጥሎ ሲሄድ፥ ጉዲፈቻ ሲሰጥ-ሲቀበል፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንደየአቅሙ በየኬላው ውሽማውን፥ እቁባቱን ሲያስቀምጥ፣ ገፋ ሲል ደግሞ እነዚህ ግንኙነቶች ወደ ፍቅር አድገው፥ በስነስርዓት ተጋብቶ ሲዋለድ በዚህ ሁሉ መሀል የምግባር፥ የእሴት፥ የቋንቋና የባህል ጋብቻ የለም ማለት አይቻልም። በተለያዩ ጦርነቶች ከክፍለ-ሀገር ክፍለ-ሀገር፥ ከወረዳ ወረዳ በሚደረጉ ዘመቻዎች ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ ወንድ ሚስትና ልጆቹን ጥሎ ሲሄድና በየቦታው ለረዥም ጊዜ ተለይቶ ሲቆይ፥ ወታደር ስለሆነ ሳይሆን ሰው ስለሆነ፥ የስጋ ፈቃዱን ማሟላት ይገደዳል። በጦርነቱ መሀል እያወቀም ይሁን ሳያውቅ እራሱን የማባዛት ግፊቱን መቀጠልም ልብ በሉ። በዚህ መሀል በየቦታው በሰፈረ ቁጥር ከአካባቢው ጋር በውጊያ ጊዜ ጭካኔ ያለውን ያህል ሰብአዊ ግንኙነቶችም ሊታሰብ በማይችል ደረጃ አዎንታዊ በሆነ መንገድ ይኪያሄዳሉ። በዚህ ዓይነት የሚገናኙ ሰዎች ደግሞ ስለ ራሳቸው ስለ አካባቢያቸውና ስለባህላቸው መወያየታቸው አይቀርም። የቤተሀይማኖት እና ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ የሀገራችን ጸሓፍት እና የውጭ ሀገር ዜጎች የመንግሥታትንና የጦርነቶችን ታሪክ ሲፅፉ፥ እኛም ያንን ስናነብና ስናወጋ፣ ከትረካው የመጎዳቱን መጠን የተረዳ ወገን ይህንን "የተዛባ ግንኙነት (ለ)ማረም" በየፊናው ሲታገልና በልዩ ልዩ ደረጃ የሚዘገብ መሰዋእትነት

**ሲከፍል፤ አሁንም የሕዝቡ ኑሮ ዝም ብሎ ሲቀጥል ይኸው ለብዙ ዓመታት ኖረ፡፡ በፊትም፥ አሁንም በሕዝቡ መሀከል የተፈጠረውን የአኗኗር ስልትና ከዚህ አኗኗር ስልት የወጡትን ልዩ ልዩ እሴቶች በወጉ የመረመርን አለን ብዬ በፍፁም አላስብም፡፡ በእኔ አስተያየት ግን በዚህ አስከፊ የጦርነት ታሪካችን ውስጥ፥ በተለይ በተርታው ሕዝብ ሕይወት ውስጥ፥ አንዳንዴ በግድ ተጀምሮ በግድ ባለቀ ፥ አንዳንዴ በግድ ተጀምሮ በፈቃድ ባለቀ፥ አንዳንዴ በፍቅራዊም ሆነ ንዋያዊ ስምምነት ተጀምሮ በፍቅር ባለቀ ማኅበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊ፥ ባህላዊና ወሲባዊ ግንኙነት ውስጥ ማንም ያልነካውና ያላጤነው፥ አብራርቶ በጥናት ያላቀረበው ሕይወታዊ እውነት አለ የሚል፥ ለብዙ ጊዜ አብሮኝ የቆየ ጠንካራ ሀሳብ አለ፡፡..."**

ይህ ጥቅስ፥ ባህል ወይም አኗኗር (ኑሮ) እኔ ለማስበው ዓይነት አንድነት ያደረገውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያመለክት ይመስለኛል፡፡ ባብዛኛው ዝም ብለን፥ የሚጠበቀውን ያህል ሳንራኮት፥ በአንድነት እስከዛሬ እንድንኖር ያስቻሉን በጥቅሱ ውስጥ ከተነገሩት የሰው-ለሰው፥ የእለት-ተእለት ግንኙነቶች፤ ባብዛኛው ኑሯቸውን ሊያሸንፉ ሲሉ ሰዎች እርስ በርሳቸው ለብዙ ዘመናት ካኪያሄዷቸው መስተጋብሮች የበቀሉ የጋራ እሴቶች ይመስሉኛል፡፡ በሂደት እየዳበሩ፥ በየወቅቱ ከሚያጋጥሙ መጠነኛና ከፍተኛ ስህተቶች እንደየሁኔታው በግድም በውድም እርስ በርስ እየተማማሩና እየተራረሙ ከነእንከናችን እዚህ ያደረሱን ይመስለኛል፡፡

ይሁን እንጂ፥ ለልማትም ሆነ ለእለት ተእለት ሕይወት ባህል ያለውን ከፍተኛ ሚና፥ የሀገሪቱ መሪዎችም ሆኑ ብዙዎቹ የተማሩ ሰዎች ተገንዝበው ሲያስገነዝቡና ለጉዳዩ ተግባራዊ ቅድሚያ ሲሰጡ አይታዩም፡፡ ስለዚህም፥ በእቅድና በእውቀት ለሚኪያሄድ ለምር (serious) የባህል ትምህርትና ምርምር ትኩረት እንዳልተሰጠ አለ፡፡ እነዚህን እሴቶች አጥንተን፥ በወጉ ተረድተንና አውቀን፥ አንድነታችንን ልናጠነክርባቸው አልቻልንም፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ የተጎዳን ይመስለኛል፡፡ ለወደፊቱም ቢሆን በሀገራችን ውስጥ የሚገኙትን ብሄረሰቦች ባህሎች በማጥናት አንድነታችንን የሚያጠናክሩትን ለይተን እያወቅን፥ በእነርሱም አማካይነት ልዩነትን የሚያከብር እና፤ መሰረቱን ግን፥ ካፍ እስከገደፍ የሞላ እኩልነትን ያደረገ አንድነትን፥ በእውቀትና በእቅድ ማልማት ያለብን ይመስለኛል፡፡

ሌላው የጥያቄህ ክፍል፥ **"ባህል ለኢትዮጵያ ህዝብ ልማት የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው?"** የሚለው ነው። ጥያቄው ጥሩ ነው፤ ግን ከባድ ጥያቄም ነው። አሁንም፥ በጥቅሉ ብቻ ልመልሰው ነው የምሞክረው። እኔ፥ "ባህል የአኗኗር ዘዴ ወይምሥርዓት ነው" በማለት ቀልጠፍ አድርገው ከሚገልፁት ሰዎች ጋር ነው የምስማማው። ለእንዲህ ዓይነቱ የእለት ተእለት ኑሮ ውይይትም የሚጠቅመው ይሄ ይመስለኛል። ይህ የአኗኗር ስርዓት ደግሞ መንፈሳዊና ቁሳዊ ጉዳዮችን ይመለከታል። ስንኖር እናስባለን፥ እንዘፍናለን፥ እናለቅሳለን ወዘተ. እኒህ የመንፈሳዊ ህይወት ገፅታ ናቸው። ምጣድ፥ ገንቦ፥ እንስራ እንሰራለን እነዚህ ደግሞ የቁሳዊ ህይወት አካሎች ናቸው ማለት ይቻላል። ልማትም እንደዚሁ መንፈሳዊና ቁሳዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ጉዳይ ነው። ስንማር ስንፈላሰፍ፥ እውቀትን ስናመነጭ፥ ልዩ ልዩ ጥበባዊ ድርሰትን ስንፈጥርና ስንከውን ለመንፈሳዊ ልማት አስተዋፅኦ እያደረግን ነው። እርሻ፥ መንገድ፥ ህንፃ ወዘተ. ስንገነባ ደግሞ ለቁሳዊ ልማት አስተዋፅኦ እያደረግን ነው። አርኪቴክቱና መሐንዲሱ ከፊታችን ሙሉ በሙሉ ባይናችን የምናየውን ለምሳሌ የሼራተንን ሕንፃ ይገነባሉ። ይህ ግንባታ ቁሳዊ ስለሆነ ዓይን ያለው ሁሉ በግዱ ያየዋል። ደራሲውና ፈላስፋው ደግሞ ልዩልዩ እሴቶችንና የሕይወት ክስተቶችን ጡባቸው፥ ብሎኬታቸውና ሸክላቸው አድርገው፥ በረቀቀ መንገድ እሰው አእምሮና ስሜት ውስጥ መንፈሳዊ ሕንፃ ይገነባሉ። ይህ ግንባታ ረቂቅ ስለሆነ በዓይን ብቻ አይታይም። ከፍ ሲል ዓይነ-ኅሊና ያስፈልገዋል። ቢያንስ ቢያንስ ግን ሕይወትን የማስተዋል፥ የማድመጥ፥ የማጣጣም ክሂል ያስፈልገዋል።

ታድያ፥ በቁሳዊና በመንፈሳዊ ሕይወቶች መሀከል ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት አለ። ነገር ግን፥ በተለይ በእንደኛ ዓይነቶቹ ሀገሮች፥ በተለይ ደግሞ ዛሬ ዛሬ፥ ስለልማት ሲወራ ስለኢኮኖሚ ልማት፥ ስለሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ብቻ ማውራት በጣም ተለምዷል። ስለቁሳዊ ልማት ነው ተጋንኖ የሚነገረው። ይህንን ቁሳዊ ልማት የሚያመጣው ግን ሰው ነው። ሀገር ያለማል የተባለው ሰው እራሱ ካልለማ ደግሞ፤ በሌላ አነጋገር፥ የተወጠነው ቁሳዊ ልማት ጠቃሚ መሆኑን ተረድቶና አምኖ በሙሉ ልቡ ወደተግባር ካልተሰማራ፤ የታሰበው ቁሳዊ ልማት በሚታሰበው ልክ ምን ጊዜም አይገኝም። ስለዚህ፥ አንድ የልማት ስራ ሲታሰብ፥ ያንንን ስራ ይሰራል ተብሎ የሚታሰበው ሰው ፍላጎት፥ እምነት፥ የሕይወት ፍልስፍና፥ የመኖሪያ አበይት እሴቶች ወዘተ. መታወቅ አለባቸው። እነዚህን ለማወቅ ደግሞ የተለያዩ ፎክሎሮቹን (ማለትም፥ ተረቶቹን፥ አፈዶዎቹን፥ ገድሎቹን፥ ተአምራቶቹን፥ እንቆቅልሾቹን፥ የሕይወት ፍልስፍናዎቹን የሽክላና የአንጥረኛ ስራዎቹን፥ ልዩ ልዩ እምነቶቹን እና አምልኮዎቹን

ወዘተ.) ማጥናት ይገባል። በዚህ መልክ፥ ባህሉን አውቆ፥ ሊሰራ የታቀደውን ስራ በዚያ ባህል ውስጥ አቀልጥፎ እንዴት ማከናውን እንደሚቻል አስቦ፥ ልማቱን የሚያከናውነውን ሰው የስራው አካል አድርጎ መራመድ ካልተቻለ የልማቱ ስራ ችግር ይገጥመዋል። በጥቅሉ ሲነገር፥ ባህል ለልማት አስተዋፅ ያደርጋል ማለት ይህ ማለት ይመስለኛል።

ለነገሩ፥ ዞሮ ዞሮ የምታለማው ሰውን ነው። በእኔ አስተያየት፥ ማልማት ማለት፥ አካባቢን (environmentን)፥ ዓለምን፥ 'ተፈጥሮን' (natureን) ሳታናጋ፥ ለሰውልጅ በሚጠቅም መንገድ መለወጥና ማደራጀት ነው። ይህ ደግሞ የማያቋርጥ ሂደት ይመስላል። ባህልም ያለማቋረጥ የሚለዋወጥ ነገር ነው። ትናንት የነበረውን ለመለወጥና ለማሻሻል የእውቀትና የመንፈስ እድገት አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ውጤቱ፥ ልማትም ባህልም ይባላል። ብዙ ጊዜ፥ "የት ጋ ቆመህ፥ የምን ባለሙያ ሆነህ?" ነው የምትናገረው ነው ነጥቡ። አንዳንዴ፥ በተመስጦ ሳስብ፥ የባህልና የልማት እሳቤ፥ ሙልጭልጭ ይሆንብኛል።

**"የወደፊቱስ አቅጣጫ ምን መምሠል አለበት?"** የሚለው ጥያቄ ከዚህ በላይ በጥቅሉ የተመለሰ ይመስለኛል። ዝርዝር ፕሮግራም እዚህ ማቅረብ አይቻልም፥ አይገባምም። እስካሁን ያልኩት ሲጨመቅ፥ ባህል ለአንድነት ከእስከዛሬው የበለጠ አስተዋፅኦ እንዲያደርግ የባህል ምርምርና ትምህርት በእውቀትና በእቅድ መኪያሄድ መጀመር አለበት የሚል ይመስለኛል። ባጫጭርና በረዥም ጊዜ ስልጠናም የባህል ሰራተኞችን አቅም መገንባት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ይህ ስልጠና እውን እንዲሆን ደግሞ፥ ከከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ስለባህልና አንድነት፥ ስለባህልና ልማት፥ ስለባህልና ትምህርት፥ ስለ ባህልና ቱሪዝም፥ ስለ ባህልና ሚዩዚየም፥ ስለባህልና ኪነጥበብ፥ ስለባህልና መገናኛ ብዙኃን ወዘተ. ውይይት የሚኪያሄድበት መድረክ አስቀድሞ ቢፈጠር ጠቃሚ ይሆናል። ከዚያ በኋላ የሚሆነውን ስንደርስበት በዝርዝር የምንነጋገርበት ቢሆንም፥ ከአንደኛ ደረጃ፥ ከሁለተኛ ደረጃና ከከፍተኛ ትምህርት ሁኔታና፣ ከመገናኛ ብዙኃን አያያዝና አጠቃቀም ሁኔታ ጋር አጣምረን ሳናስብ ስለባህል ማሰብ እንደማንችል ከወዲሁ ማስታወስ ያስፈልጋል።

**"ወጣቱስ ምን ይጠበቅበታል?"** የሚለውን ጥያቄ ጥቂት ላፍታተው። ስለየትኛው ወጣት ነው የምንነጋገረው? ስለዛሬው የከተማ ወጣት? ስለዛሬው የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወጣት? ስለነገዎቹ፥ ማለትም ዛሬ በህፃንነትና በወጣትነት ድንበር ውስጥ

ስላሉት ፈጥነው "የሚወጥቱ" ("ወጣት የሚሆኑ") ወጣቶች? ስለሁሉም?... መቼም ስለሁሉም መናገር ይከብዳል። ምክንያቱም፥ በመጀመሪያ፥ ስለእያንዳንዳቸው ሀገር-አቀፍ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ፥ አስተያየቴን የምሰነዝረው ይህ ጥናት ባልተኪያሄደበት ሁኔታ ነው ማለት ነው።

የሀገሪቱ ወጣት ለኢትዮጵያ አንድነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲያደርግ እስከዛሬ ከተሰጠው ትምህርት፥ ከተሰጠው ትኩረት እና ከተሰጠው ጥቅም በጣም የተሻለ ትምህርት፥ በጣም የተሻለ ትኩረት እና በጣም የተሻለ ጥቅም ሊሰጠው ይገባል ብዬ ከምር አስባለሁ። የሀገሪቱ አቅም በሚፈቅድበት ሁሉ፥ እነዚህ ከተሟሉለት ከእስከዛሬው በላቀ ሁኔታ ጠንካራ የአንድነት ኃይል ይሆናል። እንዲሁ በደፈናው፥ "ለሀገር መሰዋት! ለሀገር መሞት! ለሀገር መስራት! ለሀገር አንድነት መቆም!" እያሉ መፈክር ብቻ ማሰማት ወደፊት ብዙ ተቀባይ ላያገኝ ይችላል የሚል ሃሳብ አለኝ።

ስለዚህ፥ በመጀመሪያ እራሱን እየጠቀመ ማኅበረሰቡን ሊጠቅም የሚችልባቸውን መንገዶች ባስቸኳይ ቀይሶ ባስቸኳይ መተግበር ያስፈልጋል። ለምሳሌ፥ በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ክፍሎች አልፎ ዛሬ በየቤቱና በየመንገዱ የፈሰሰውን ስራ አጥ የገጠርና የከተማ ወጣት አጫጭር ስልጠና እየሰጡ ሀገሪቱን የወረረችትን ወባን፥ ኤይድስን እና ቆሻሻን እንዲዋጋ፤ አልፎ አልፎ በቴሌቪዥን የምናየውን የተራቆተ አካባቢን ካስፈለገ በኮንትራት እንዲያለማ ማዝመት ይቻል ይመስለኛል። እነዚህ መሰረታዊ ችግሮች ናቸው። የማኅበረሰቡ አባል ስለሆነ እነዚህ ችግሮች የእርሱም ችግሮች ናቸው። ተገቢው ስልጠና ተሰጥቶት፥ በደሞዝ ተቀጥሮ፥ እነሱን በመዋጋት ላይ ቢሰማራ ስራ በመያዙ ይጠቀማል። እነሱን የሚዋጋ ኃይል በመሆኑ እራሱን ከጥቃት ክልል ያወጣል። ሌላውን ማኅበረሰብም ከእነዚህ አደገኛ ጠንቆች ይከላከላል።

ለዚህ የሚሆን በጀት ደግሞ የሚጠፋ አይመስለኝም። ሰሞኑን፥ ከዓለም ባንክ ለኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ከተገኘው በስራ ላይ የዋለው ዝቀተኛ መሆኑን ሰምተናል። ሌላ ጠቀም ያለ ገንዘብ በቅርቡ ይመጣልም ይባል ነበር። የተባለውን ገንዘብ ብቻ ይዞ በመነሳት እንኳ ብዙ ቁምነገር መስራት የሚቻል ይመስለኛል። ከፍ ብዬ ከጠቀስኳቸው ችግሮች ብዙዎቹ መሰረታዊ የጤና ጠንቆች ስለሆኑ፥ የኤይድስን መሰራጨትም በተለያዩ መንገዶች የሚያባብሱ ስለሆኑ፥ ለኤይድስ በመጣው ገንዘብ እነርሱንም መዋጋት ትክክል የሚሆንበት መንገድ መኖሩ በግልፅ የሚታይ ይመስለኛል። ስለዚህ፥ በነዚህ መስኮች አጭርና ጥብቅ ስልጠና፥ በልዩ ትኩረት እየሰጡና ሰልጣኙ ኑሮውን የሚደጉምበትን መንገድ እያመቻቹ ይመስለኛል፤ ወጣቱ በሀገር ግንባታ ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ሚና በተከታታይ መቅረፅና መተግበር የሚገባ። በመጀመሪያ ወጣቱ የማን እንደሆነ

በደንብ ይወቅ፥ ከልብም ይመን፡፡ "የእኔ ነህ!" የሚለው ወገን ደግሞ፥ በወግና በዲስኩር ሳይሆን በተግባር የእርሱ መሆኑን ያሳየው፥ ያሳምነው፡፡ ይህንን ማድረግ የተቀናጀ እውቀትና ልምድ ይጠይቃል፡፡ አንዴ በትክክል መፈፀም ከተጀመረ ግን፥ ከዚያ በኋላ ያለው እዳው ገብስ እየሆነ ሊሄድ ይችላል፡፡

በልጅነት የእድሜ ክልል ባሉትም ላይ፥ በእውቀትና ልምድ በተቀናጀ ስልት፣ በቤተሰብ፥ በትምህርት ቤትና በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት መዝመት ያስፈልጋል፡፡ በእነዚህ በሶስቱ መንገዶች ተሰናኝቶ፥ ባንድ ጊዜ ካልተጀመረ ተስፋ የሚሰጥ ውጤት ማየት እንጀምራለን ብዬ አላስብም፡፡ ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ፥ የዛሬ 48 ዓመት ገደማ እንዳስተዋሉት ቤተሰብ ያስተማረውን ትምህርት ቤት ካፈረሰው፥ ትምህርት ቤት የተማረውን ቤተሰብና የሚኖርበት አካባቢ ሕይወት ካፈረሰው የህፃኑ ጨቅላ አእምሮ፥ መጥፎና መልካም ልማድ "የሚዋጉበት የጦር ሜዳ" ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጦርነት ደግሞ እንኳን ለእምቦቀቅላው ህፃን ለአዋቂም እንደማይበጅ፥ በተለይ ባለፉት 30 ዓመታት የተገነዘብን ይመስለኛል፡፡ ስራው ቀላል አይደለም፡፡ ነገር ግን፥ እውቀትን፥ ልምድንና በጎ ፍላጎትን መሰረት አድርጎ መታቀድና ስራውም መጀመር አለበት፡፡ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በመግባባት ላይ የተመሰረተ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላም ብዙው ነገር ለማኅበረሰቡ ምክክር መተው ያለበት ይመስለኛል፡፡

ወጣቱም ቢሆን ስለራሱ፥ በራሱ ማሰብና መተግበር የሚችላቸውን ጉዳዮች እያሰበ መፈፀሙን መቀጠል አለበት፡፡ እስካሁን ብዙ አስደሳች ጥረቶችን ማድረጉን በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ተመልክቻለሁ፥ ሰምቻለሁ፥ አንብቤያለሁ፡፡ ትእግስቱንም ጥረቱንም ያደነቅሁባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡ ስለኢትዮጵያ ወጣት የፈጠራ ችሎታና፥ ከሰርቆ መብላት ይልቅ ሰርቶ ለመብላት የሚሰጠውን አክብሮት ለመረዳት የኢትዮጵያን መንገዶች ልብ ብሎ ማጤን የሚበቃ ይመስለኛል፡፡ ከናፕኪን እስከ ሙሉ ልብስ ቸርቻሮ፥ ጫማ ጠርጎ፥ ጋዜጣና ሎተሪ ሸጦ፥ ሳንቲም መንዝሮ፥ ትምህርት ቤት ወደሚባሉትም ሄዶ ወዘተ. ኑሮን ለማሸነፍ በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ የፈሰሰው አብዛኛው ወጣት ነው፡፡ በአዲስ አበባ መንገዶች ስንጓዝ የምናያቸው ቁጥራቸው እየጨመረ የሄዱ የእንጨትና የብረታ ብረት መስሪያ ጥጋ ጥጎችም ወጣቱ ትውልድ ሰርቶ ለመኖር የሚያደርገውን ትግል የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ብዙ እንደዚህ ዓይነት ምሳሌዎችን አጥንቶ ረዘም ያለ ገድል ሊፃፍለት የሚገባ ወጣት ብዙ ይመስለኛል፡፡ ይህ መቀጠል አለበት፡፡

እንዲቀጥልም የመንግስት ድጋፍ ያስፈልገዋል። የመንግስት ብቻም አይደለም ድጋፉ መሆን ያለበት። ንዋይ ያለው በንዋዩ፥ ሃሳብ ያለው በሃሳቡ የየበኩሉን ትብብር ሊያደርግ ይገባል። የመረዳዳቱ ስራ ሲጀመር አነስተኛም ሊሆን ይችላል። አንድ ስርዓት ወይም ድርጅት ያለው ቢሆን ግን ይመረጣል። በተለመደው፥ በየመንገዱና በየቤተፀሎቱ ይኪያሄድ በነበረው የልመና ስርዓት ዓይነት ላንዳንድ ግለሰቦች በመመፅወት፤ የምፅዋቱንም ስነስርዓት በመገናኛ ብዙኃን በማስተላለፍና ልመናን የሚያበረታታ የንግድ ማስታወቂያ በሚመስልበት መንገድ ባይሆን ይመረጣል። የምር እንነጋገር ከተባለ፥ ሁሌ ከአፉ ላይ ተመጥጦ እንዲያልቅ ከንፈሩን እያስመጠጡ፥ ሆዱን እያባቡ፥ አንጀቱን እያንቦጫቦጩ፥ "አንተም አንድ ቀን ምፅዋት ይደርስሃል!" የሚል ዓይነት አጉል ተስፋ እያስጨበጡ ብቻ፥ የአንድን ሀገር ሕዝብ ተቁምነገር ቦታ ማድረስ አይቻልም። ያልደረሰውም፥ አንድም፥ እንዲህ ዓይነቱ አኪያሄድ በየዘመኑ መልኩ እንጂ መሰረቱ ስላልተለወጠ፥ ስላልተነካ ሳይሆን አይቀርም። ጥቂት የማይባሉ ኢትዮጵያውያን ድርጅት አቋቁመው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን እያየን ነው። ከመሀከላቸው አንዳንዶቹ በድርጅት መረዳዳት ቀስበቀስ እራሱ የልማት እንቅስቃሴ ያህል ሕዝብንም ሀገርንም ሊጠቅም እንደሚችል የተገነዘቡ ይመስለኛል። በግል መረዳጃንም ይሁን ምፅዋትን የሚያስተባብሩ ሰዎች ሲያልፉ ሁሉ ነገር አብሯቸው እንደሚያልፍ፤ መረዳጃቸው በይፋ በታወቀ ድርጅቶች በኩል ከተኪያሄደ ግን ግለሰቦቹ ቢያልፉም ስራው እንደሚቀጥልም የተገነዘቡ ይመስለኛል። የምር መስራት የምር ከመነጋገር እጅግ ይከብዳል። ለዚህም ይሆናል፥ አንጀት ወደሚበሉና ብልጭ ብለው ወደሚጠፉ፥ መሰረታዊውን ችግር ወደማይነኩ ተግባራት ሰዎች በቀላሉ የሚሳቡት።

ብቻ፥ ሃሳብ ያለው በሃሳብ፥ ንዋይ ያለው በንዋይ የምር መርዳቱ የየግለሰቡ የውዴታ ግዴታ ይሁን። ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸውን ምክንያቶች ሰምቶ የማይተባበርም ካለ፥ ለራሱ ሲል እንዲተባበር እንዳሳስበው መልካም ፈቃዱን እጠይቃለሁ። ትእግስት ሁሉ ዘላለማዊ አለመሆኑንም ላሳስበው እወዳለሁ። ትእግስት፥ ቀስ እያለ፥ በተለያዩ መንገዶች ይሸረሸር፥ ይሸረሸርና አንድ ቀን ያፈተልካል። ሲያፈተልክ ለብዙዎች ከመነሻው አይታይም። እየቆየ መታየት ሲጀምርም እንኳ እያዩ ችላ ማለት፥ ወይም ዓይን መጨፈን በብዛት አለ። ነገሮች ሲባባሱ ግን ሁሉም የማኅበረሰብ አባል በግዱ ያየዋል። ያኔ መንጫጫት ይጀመራል። በእኔ አስተያየት ያኔ ከመጮህና ከመንጫጫት ዛሬ፥ ሁሉም በሚችለው ሁሉ ስርዓት ባለው መንገድ መንቀሳቀስ ቢጀምር ይሻላል። ኋላ መዋከብና መንጫጫት ምንም ዋጋ አይኖረውምና።

ፈቃደ አዘዘ                                        መጋቢት 27 ቀን 1996

## 6. በአገራችን ባህልና ስፖርት ለሠላም፥ ለመቻቻል፥ ግጭትን ለማስወገድ፥ ተቀራርቦ ለመወያየት፥ ለልማት ጥረትና ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ያላቸውን ሚና ከወጣቱ ትውልድ አንፃር እንዴት ማየት ይቻላል?

ይኼም ከባድና ውስብስብ ጥያቄ ነው:: ... ግን ዝም ብዬ በድፍረት ልሞክረው? ... ዛሬ፥ በሕይወት ከሚሆነው ጋራ የማይጣጣሙ ብዙ ነገሮች በዓለማችን ይነገራሉ:: ከነዚህ ጎራ የሚመደቡ፥ ከስፖርትና ከባህል ጋር የተያያዙ ብዙ ንግግሮችና መፈክሮች አሉ:: እነርሱ የብዙዎቻችንን አስተሳሰብና አኗኗር አሉታዊ በሆነ መንገድ እየተጫኑ ይመስለኛል:: እስቲ፥ ለሁላችንም ግልፅ የሆኑ ምሳሌዎችን ከስፖርትም ከባህልም ልግለፅ::

ዛሬ፥ በዓለም ላይ በስፋት የተንሰራፋው የእግር ኳስ ጨዋታ፥ ጥያቄህ ውስጥ ለተዘረዘሩት መልካም ቁምነገሮች ቢውል ሁላችንም ደስተኞች እንሆናለን ብዬ እገምታለሁ:: ... እኔ በጣም ደስተኛ እንደምሆን ጥርጥር የለውም:: (በነገራችን ላይ፥ የአዲስ አበባ ስታድዮም ኳስ ከእንዲህ ዓይነቱ ስሜት እየራቀ የሄደ ሲመስለን ጭምር ነው ከጓደኛዬ ጋር መግባት ለማቆም የወሰንነው...) ዓለማቀፋዊው ሁኔታ ግን የእኛን ፍላጎት እያሟላ ከመሄድ ይልቅ ስጋታችንን እና ንዴታችንን እየጨመረ የሚሄድ ይመስላል::

የጋጠወጥ ተጫዋቾችና ተመልካቾች ብዛት በዓለም ስታድዮሞች እየጨመረ ነው:: ሀገር-ዘመት ዋልጌ ተመልካቾች የስፖርቱን መልካም ስምና ዝና እያጎደፉት ይገኛሉ:: በዚህም ለሰላም፥ ለመቻቻል፥ ግጭትን ለማስወገድ ወዘተ. የሚሉ መልካካም ቃላት በተቃራኒ ተግባር መታጀባቸው እየጨመረ ሲሄድ ይታያል:: እንዲያውም፥ በየትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው ስሜት የተገፋፉ ጭፍን የማሸነፍ ፍላጎት፥ የክለብ መሪዎች፥ የባለንብረቶች፥ የደጋፊዎችና የተጫዋቾች ብቸኛ ዓላማ እየሆነ የመጣ፤ ስፖርቱና ወንድማማችነቱም እየተናቀ የሄደ ይመስላል:: በአፋቸው፥ "ማሸነፍና መሸነፍ በስፖርት ዓለም ያለ ነገር ነው" ቢሉም ተግባራቸው የንግግራቸውን ያህል ጎልቶ አይታየኝም:: "አሰልጣኞች፥ ማኔጆሮች፥ ተጫዋቾች፥ ደጋፊዎች ጨዋታ ባለ ቁጥር የጨዋታውን ውበት ነው የሚያደንቁት ወይስ ውጤቱን ነው የሚያሰላስሉት?... በስፖርቱ አማካይነት ወንድማማችነትንና ፍቅርን ነው የሚያዳብሩት ወይስ ማን እንደኔነትን እና ንግድን ነው የሚያፋፍሙት?..." ተብዬ ብጠየቅ መልሴ ግልፅ ነው:: ጥቂት

የማይባሉት፥ ከንፈርና ምላሳቸውን ከማስቲካ ጋር የሚያኝኩ እስኪመስሉ ድረስ በጭንቀት ተወጥረው የሚጠብቁት፥ ውጤትን፥ ከውጤትም ማሸነፍን ብቻ እየመሰለኝ ከመጣ ቆይቷል። ከስፖርት ይገኛል የሚባለው መፈቃቀርና ወንድማማችነት ወደ ጎን ተትቶ፥ ሁሉም የየራሱን ዓይነት አምባገነንነት ለማስፈን የሚያደርገው ፋክክር እያየለ የመጣ ይመስላል። ንግዱም ዓይን አውጥቶ ከመጠን በላይ የተጧጧፈ ይመስላል። የዚህ ዓይነቱ መንፈስ፥ ያቅሙን ያህል፥ ግን ደግሞ ባልታሰበ ፍጥነት ወደእኛም ሀገር እየተዛመተ ነው። ያፋጠነው፥ የግሎባላይዜሽን እኩይ አስተዋፅኦ ጭምር ነው የሚል ግምት አለኝ። እንዲህ ዓይነቱ መንፈስ፥ ለልማትም፥ ለሰላምም፥ ለመቻቻልም፥ ግጭት ለማስወገድም የሚበጅ አይመስለኝም።

ስለዚህ፥ ከወጣቱ በፊት፥ የሀገሪቱ (ነገሩ የዓለምንም በዋናነት ይጨምራል) የስፖርት አመራር በምግባር የታነፀና የስፖርቱንም ሂደት በእውቀት፥ በስነስርዓት፥ በስነምግባር እና በሕግ ሊመራ የሚችል ሊሆን ይገባል። ወጣቱ ትውልድ፥ ባብዛኛው ያገኘውን ይዞ ነው የሚሄድ። በስነስርዓት የሚኪያሄድን መልካም ነገር ሆነ ብሎ ለማፍረስ የሚሽቀዳደም አይመስለኝም። ስለዚህ ስነምግባሩ፥ ስነስርዓቱ፥ በእውቀትና በሕግ መስራቱ፥ ባጠቃላይ አነጋገር መልካም አርአያነቱ፤ በስፖርት መሪዎች፥ በአሰልጣኞች፥ በተጫዋቾች፥ በጋዜጠኞች እና በጎልማሳና በአዋቂ ተመልካቾች ዘንድ ከሰፈነ ወጣቱ ትውልድ ይህንኑ የሚያዳብር ይመስለኛል።

በባህልም በኩል እንዲሁ የሚያሳስብ ነገር አለ። **"ዓለም ወደ አንድነት እየመጣ ነው። ልዩነቱ እየጠበበ ነው። ሰዎች ከመቼውም በላይ እየተቀራረቡ ነው። የሰዎችን ወንድማማችነትና ፍቅር ግሎባላይዜሽን እያሰፋ ነው። በዓለም ላይ የሚሰራጩ ዜናዎች፥ የጥበብ ስራዎች፥ ዘፈኖች እየተመሳሰሉ መጥተዋል፥ መረጃዎች በፍጥነት እየተዛመቱ ነው ወዘተ. " ይ ባ ላ ል**። በዚህ ሁሉ መሀከል ግን የማይነገር ዓቢይ ቁምነገር አለ። በጥያቄ መልክ ላቅርበውና መልሱን ለሁላችንም ልተው።

"ዜናው ስለማን ጉዳይ ነው? ዜናውን የሚመርጠው ማን ነው? የሚተላለፈው በማን የቴሌቪዥን ጣቢያ፥ በማን የመረጃ መረብ (ዌብሳይት) ነው? የሚሰራጨው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትና የዋልታ ዜና ነው ወይስ የሲ.ኤን.ኤን እና የቢ.ቢ.ሲ? ለምን? የማን ዘፈን ነው በዓለም ላይ በቀላሉና እንደልብ የሚሰራጨው? የአሜሪካና የእንግሊዝ ሙዚቃ ነው ወይስ የሀመር፥ የአማራ፥ የኦሮሞ፥ የወላይታ፥ የሲዳማ ወዘተ. ዘፈን ነው? በቀላሉ የምናገኛቸውና እንደልብ የሚሰራጩ ዘፈኖች፥ ዳንሶች፥ ፊልሞችስ

ምን ዓይነት ናቸው? በቪድዮ፥ በሲዲ፥ በቴሌቪዥን ተደጋግመው የሚረጩት የትምህርት ፕሮግራሞች ናቸው? በመንገድና በድልድይ ምህንድስና የሰውልጅ ስለደረሰበት ደረጃ፥ በቀዶ ጥገና ህክምና ስለመራቀቁ፥ በመጠነኛ የእርሻና የኢንዱስትሪ መሳሪያዎች በየመንደሩ ስለሚኪያሄዱ አስደናቂ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩ ናቸው? ወጣቱን ትውልድስ በዚህ አቅጣጫ እየጎጓ እንዲያስብ፥ እንዲመኝ፥ እንዲሰራ የሚያደርጉ ናቸው? ወይንስ በወሲብና በሀሺሽ እንዲናውዝ በትጋት የሚያነሳሱት ናቸው እንደልብ የሚረጩት? ኧረ ለመሆኑ እነዚህ ፕሮግራሞች የማን ናቸው:: ለምንስ ነው እንዲህ በርካሹ የተለቀቁብን? የሚቀበላቸውስ ማን ነው? በሀገሩ የቴሌቪዥንና የሬድዮ ፕሮግራም ተቀብሎ በእንክ-እንክ እያቆላመጠ የሚያሰራጫቸው ማን ነው? ለምን? በሳምንት የሚረባ ጊዜ ለምር (serious) የባህል፥ የስእል፥ የሙዚቃ፥ የፊልም፥ የትያትርና የስነፅሁፍ ውይይት በቋሚነት የማይሰጥ ሬድዮ ጣቢያስ እንዴት ነው ስለውጭ ሀገር እግር ኳስ ባንድ ፕሮግራም ብቻ፥ በተከታታይ የሶስት ሰዓት አየር ጊዜ የሚሰጥ? እንዴትስ ነው በዚያው ጣቢያ የሚተላለፈውን ስለኤይድስ የተዘጋጀ አጭር ፕሮግራም ገንዘብ የሚያስከፍለው? ለምንድነው ከውጭ ስለሚመጣ ነገር ብቻ ልክ-የለሽ የሚባል ጊዜና ዝርዝር፥ ጥቂት ለማይባል ጊዜ ደግሞ አልባሌ መረጃ የሚሰጥ? እዚህ ሁሉ ውስጥ ብዙ ምስጢር ያለ ይመስላል::

አንዳንድ ሰዎች ይሄንን ሁሉ ግሎባላይዜሽን እያቀራረበን ነው በሚል በቀቀናዊ መፈክር ሊቋጩት ይሞክራሉ:: ግሎባላይዜሽን ሁላችንንም እያቀራረበ ነው ማለት ግን ምን ማለት ነው? እኔ የሌላውን ባህል ብቻ የምቀበልበትና በእጅ አዙር የምጋትበት፥ የእኔን ባህል ግን የእኔን ገፅታ (image) በማይበድል ወይም ከሌላው አስበልጦም እኔን በማይጠቅም ምጣኔ የማላቀብልበት ሁኔታ እንዴት ፍትሓዊ ሊሆን ይችላል?

ይህንን ሁሉ ያነሳሁት፥ "በአገራችን ባህልና ስፖርት ለሠላም፥ ለመቻቻል፥ ግጭትን ለማስወገድ፥ ተቀራርቦ ለመወያየት፥ ለልማት ጥረትና ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ያላቸውን ሚና ከወጣቱ ትውልድ አንፃር እንዴት ማየት ይቻላል?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፥ አንድ ቁልፍ የሆነው መገናኛ ብዙኃን፥ ምን ያህል ምርኮኛ እንደሆነ ባጭሩ ለመጠቆም ነው:: በጥያቄው ውስጥ የተዘረዘሩትን እሴቶች በወጣቱ መሀል ለማስረፅና የተጠቀሱትን ተግባራት ለማከናወን መገናኛ ብዙኃን ትልቅ ሚና አላቸው:: አሁን ባሉበት ሁኔታ የተዘረዘሩትን ተግባራት አዎንታዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚችሉ አይመስለኝም:: ስለዚህ በዚህ ኢንተርቪው ውስጥ ቀደም ብዬ እንደጠቆምኩት፥ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን በሚችሉበት መንገድ መሻሻል

ያለባቸው ይመስለኛል። እነዚህን እሴቶች ለዘለቄታው የማስረፅ ጉዳይን በሚመለከት ከዚህ በላይ የጠቋቆምኳቸው ነጥቦች ስላሉ አንባቢዎቼን ወደእነርሱ መርቼ፥ የዚህን ጥያቄ መልስ በዚሁ ባበቃ የሚሻል ይመስለኛል።

## 7. ባሁኑ ጊዜ ወጣቱ ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በመታደግ የወጣቱን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ደረጃ በደረጃ ለማረጋገጥ ምን መደረግ አለበት?

ከዚህ ጥያቄ ጋር የተያያዙ ብዙ መሰረታዊ ነጥቦች ከዚህ በላይ የተነካኩ ይመስለኛል። ምክንያቱም የቀረቡልኝ ጥያቄዎች በጣም የተያያዙ ወይም ተቀራራቢ ናቸው። አንዱ ሲመለስ ሌላውም መነካካቱ የቀረ አይመስለኝም። ቢሆንም ሶስት ዓቢይ ነጥቦችን ብቻ ልጥቀስ። ሌላው ቢቀር እስካሁን የተባለውን ያጠናክራሉ።

"ባሁኑ ጊዜ ወጣቱ ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በመታደግ የወጣቱን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ደረጃ በደረጃ ለማረጋገጥ"፡-

ስለ ትምህርት ልዩ ልዩ የድል አታዝ ብቻ መጥቀስ የትም እንደማያደርስ አውቀን አኪያሄዳችንን በእውቀት መመርመርና ያገኘነውንም ውጤት ተግባር ላይ ማዋል ይገባናል። እዚህ ክፍል፥ እዚያ ደረጃ ደረሱ ብሎ መቁጠርም የትም አያደርስ። በሆነ ዓላማና ቁምነገር ላይ ያነጣጠረ ቀልጣፋና ያልተልፈሰፈሰ ትምህርት መስጠት ያሻል። ወይ ጠቃሚ አጠቃላይ ትምህርትና፥ ጠቃሚ የሙያ ትምህርት መስጠት ላይ አነጣጥሮ ያንን ማከናወን። ወይም ደግሞ የተራቀቁ የዩኒቨርሲቲ ምሁራንን አፍርቶ ሀገርን እንዲያለሙ፥ ባለምም ላይ በእውቀታቸው ተፎካክረው ሰርተው እንዲኖሩና ለሀገራቸውም ገቢ እንዲያስገኙ ማድረግ። ወይ ሁለቱንም ማድረግ። ይህ ሁሉ ደግሞ በነፃ ስለማይገኝ አንድ ውሳኔ ከመወሰን በፊት ማሰብ ያስፈልግ ይመስለኛል። ብቻ፥ ሀገሪቱ ያሏትን የእውነት መምህራን እና በልዩ ልዩ ሙያዎች የተካኑ ፕሮፌሽናሎቿን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር አሰባስቦ አስቸኳይ የጠቃሚ ትምህርት "ዘመቻ" **በእውቀትና በስርዓት አቅዶ ማኪያሄድ ያስፈልጋል**። በእኔ አስተያየት፥ የትምህርት ስርዓታችን ልዩ አጣዳፊ ህክምና ያስፈልገዋል። ያለትክክለኛ ትምህርት ማንንም መታደግ ስለማይቻል ነው ይህንን ነጥብ አስቀድሜ ያነሳሁት። ተሳስቼ ከሆነ ደስታው የእኔ ነው።

መገናኛ ብዙኃን በተለያየ መንገድ ከሚጫወቱት የማደንዘዝ ሚና ይልቅ በስርዓት የማዝናናት፥ የማስተማር እና ለቁምነገር የማነቃቃት ሚናቸው እንዲጎለብት እስካሁን ከሚያደርጉት ጥረት የበለጠ፥ እጅግ የበለጠ ጥረት ማድረግ የሚገባቸው ይመስለኛል። በእኔ አስተያየት፥ ይህ ተግባር፥ በእውቀት፥ በመጠነኛ ቅን አመለካከትና ዕኑ ፍላጎት ባጭር ጊዜ ሊከናወን ይችላል።

ተደጋግሞ እንደተነገረው፥ ብዙው ወጣት ማንበቢያና ማጥኛ ቦታ ያስፈልገዋል። መዝናኛ ቦታና መሮጫ ሜዳም ያስፈልገዋል። እውስጡ ያለውን እምቅ ኃይል የሚያቃጥልበት፥ የሚያስተነፍስበት ቦታ ያስፈልገዋል። ይህንን ቦታ ካጣ ይህንን ኃይል በቡድን ጠብና ድብድብ እንዲያስወጣ እምቅ ኃይሉ ይገፋፋዋል። በልዩ ልዩ የወንጀል ድርጊቶች እንዲያስወጣውም የሚገደድበት ጊዜ ይኖራል። ይህ ሁሉ ለወጣቱም፥ ለማኅበረሰብም፥ ለሀገርም፥ ለመንግስትም አይጠቅምም። በዚህ ደግሞ፥ የሀገሪቱን መነሳቆል ከሚፈልጉ ወገኖች በስተቀር ሌላ የሀገር ውስጥ ተጠቃሚ ወገን የለም ማለት ነው። ስለዚህ አንድ ነገር ባስቸኳይ መደረግ አለበት እላለሁ። ስብሰባ፥ ኮንፍረንስ፥ ወርክሾፕ፥ ሲምፖዝየም፥ ሴሚናር፥ ጥናት፥ "ፓናል ውይይት" ወዘተ ይደረግ ማለቴ አይደለም። በጭራሽ!!! ቢያንስ ቢያንስ በዘመነ ደርግ የመጀመሪያ አጋማሽ በብዙ ቀበሌዎች ተከፍተው የነበሩትን ቤተመፃህፍት፥ የመዝናኛ ስፍራዎችና መሳሪያዎች፥ አዳራሾች፥ ከጊዜው ሁኔታ ጋር አጣጥሞ፥ እንደገና ማደራጀት ማለቴ ግን ነው። ለትያትር፥ ለሙዚቃ፥ ለስእል፥ ለውይይትና ለስነፅሁፍ ክበባት መድረክ መስጠት ማለቴ ነው። ዛሬ በብዛት የበቀሉትን የኤይድስ፥ የአካባቢ (environment) ጥበቃና ልማት፥ የአካባቢ ፅዳት ወዘተ ክበባትንም ከየቀበሌው ነዋሪ በጎ ፈቃድ በመነጨ ተሳትፎ እያጠናከሩ ቦታና ድጋፍ መስጠት ይጠቅማል ባይ ነኝ።

በመጨረሻ ባህል ብቻውን ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል ለማሳሰብ እወዳለሁ። ብቻውን አንድነትን እና ልማትን ሊያጠናክር አይችልም። በሌሎች ማኅበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችም መታገዝ አለበት። እነርሱ ግልፅ፥ ፍትሐዊ፥ ስርዓታዊና ለማኅበረሰባቸው አዎንታዊ ፋይዳ ባለው መንገድ ጠንካራ ከሆኑ፥ ባህልም ይህንን ጥንካሬ ይበልጥ ያጠናክራል። እነርሱ ጠንካራ እንዲሆኑ ግን በሚቀይሷቸው ፖሊሲዎች እና በሚያከናውኗቸው ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ባህል ሊያደርግ የሚችለውን አስተዋፅኦ ተምር መመርመርና፥ ተቁምነገር መጣፍ አለባቸው። ይህንን መስተጋብር ሁሌ ልብ ማለት ጠቃሚ ይመስለኛል- ምስጋና ለዲያሌክቲክስ!

---

ፈቃደ አዘዘ
በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለትምህርት መምህር
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
መጋቢት 27 ቀን 1996